# ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን
# ሁለተኛ ክፍል



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ የመንበረ ፓትርያርክ (ዓለም አቀፍ) የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት የተዘጋጀ

# ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን
# ሁለተኛ ክፍል

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ የመንበረ ፓትርያርክ (ዓለም አቀፍ) የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት የተዘጋጀ 2015 ዓ.ም

## ማውጫ


ምዕራፍ አንድ፡ ቤተ ክርስቲያን የመግባት ሥርዓት..... ፩

፩.፩ ቤተ ክርስቲያን የመግባት ሥርዓት......... ፪

፩.፪ ቤተክርስቲያን የመሳለም ሥርዓት........... ፮

፩.፫ የስግደት ሥርዓት .................. ፯

፩.፬ ነጠላ የመልበስ ሥርዓት............... ፰

ምዕራፍ ሁለት፡ ሥርዓተ ቅዳሴ.................. ፲፫

፪.፩ የቅዳሴ ሥርዓት ......................... ፲፭

፪.፪ ቅዳሴ ውስጥ መሳተፍ የሚገባቸው እነማን ናቸው..... ፲፭

፪.፫ በቅዳሴ ወቅት ስለሚደረጉ ሥርዓቶች .............. ፲፭

፪.፬ በቅዳሴ ወቅት የሚከለከሉ ድርጊቶች ............... ፲፯

ምዕራፍ ሦስት፡ ቅዱስ መስቀል ................. ፲፱

፫.፩ መስቀልና ክብሩ .................. ፳

፫.፪ ቅዱስ መስቀል ስለመሳለም .................... ፳

፫.፫ መስቀል በአንገታችን ለምን እናሥራለን?........ ፳

ምዕራፍ አራት፡ ሥርዓተ ቍርባን .................... ፳፫

፬.፩ ሥርዓተ ቍርባን በቤተክርስቲያን ............ ፳፬

፬.፪ እንዴት መቍረብ እንዳለብን.................... ፳፮

፬.፫ ሥጋ ወደሙ ለሰው ልጅ የሚሰጠው ጥቅም........ ፳፯

ምዕራፍ አምስት በዓላት .................. ፳፱

፭.፩ የበዓላት አከባበር ሥርዓት በቤተክርስቲያን ......... ፴

፭.፪ በዓላትን እንዴት እናከብራለን .......... ፴፫

፭.፫ በዓላት የማክበር ጥቅም ........... ፴፭

ዋቢ መጻሕፍት ...................... ፴፮

# መግቢያ

ሥርዓት "ሠርዐ" ሠራ ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ደንብ፣ አሠራር፣ መርሐ ግብር ማለት ነው። ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ስንልም የቤተክርስቲያን ዕቅድ፣ የቤተክርስቲያን አሠራር፣ መርሐ ግብር ወይንም ደንብ ማለታችን ነው።

በዚህ የክፍል ደረጃ ተማሪዎች ማወቅ አለባቸው ተብሎ ከሚታሰበውም በላይ ያወቁትን ሥርዓት ተግባራዊ እንዲያደርጉ በማሰብ የቤተክርስቲያን ሥርዓት ለዕድሜአቸው በሚመጥን መልኩ ከብዙ በጥቂቱ ተዘጋጅቷል።

መጽሐፉ በአምስት ምዕራፎች የተከፈለ ሲሆን በእያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ ብዙ ንዑሳን ርዕሶች አሉት።

- ምዕራፍ አንድ ቤተክርስቲያን የሚገባ ማንኛውም ሰው ምን ማድረግ እንዳለበትና ምን ዓይነት ሥርዓት መከተል እንዳለበት ያትታል፣
- ምዕራፍ ሁለት ስለ ሥርዓተ ቅዳሴ፣
- ምዕራፍ ሦስት ስለ መስቀልና ክብሩ፣
- ምዕራፍ አራት ሥርዓተ ቊርባን
- በመጨረሻም በምዕራፍ አምስት የበዓላት አከባበር ሥርዓትን አካትቶ ተዘጋጅቷል።

# ምዕራፍ አንድ
# ቤተ ክርስቲያን የመግባት ሥርዓት

## የምዕራፉ ዓላማ

**ልጆች ይህንን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ**

- ቤተክርስቲያን ማለት ምን ማለት እንደሆነ፤
- ወደ ቤተክርስቲያን ሲገቡ ከውጪ በር ጀምሮ ምን አይነት ሥርዓት ማከናወን እንዳለባቸው ይረዳሉ፤ የተረዱትንም ተግባራዊ ያደርጋሉ፤
- ቤተክርስቲያን ከገቡ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለባቸውና ምን ማድረግ እንደሌለባቸው በሚገባ ይገነዘባሉ።

## ቁልፍ ቃላት

- ጸዓዳ ፡- ነጭ የሆነ
- ዘይቤያዊ ፦ አገባባዊ

## የማስጀመሪያ ጥያቄዎች

- ቤተክርስቲያን የምንላቸው እነ ማንን ነው?

ልጆች ቤተክርስቲያን ስንል ሦስት ዘይቤያዊ ፍቺዎች አሉት። እነዚህም፡-

- አንድ ክርስቲያን የሆነ ሰው፤
- የክርስቲያኖች ኅብረት፤
- ሕንፃ ቤተ-መቅደስ ናቸው። በዚህ ትምህርት ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ለቤተ ክርስቲያን ከተሰጡት ፍቺዎች መካከል "ሕንፃ ቤተክርስቲያን" ሕንፃ ቤተክርስቲያን ወይም ቤተ መቅደሱን ማለታችን ነው።

## ፩.፩ ቤተክርስቲያን የመግባት ሥርዓት

### ፩.፩.፩ ቤተክርስቲያን ከመግባታችን በፊት የሚደረግ ዝግጅት

ቤተክርስቲያን ሕይወትን የምናገኝባት የሕይወት ቤት ናት ከዚህ አንጻር ቤተ ክርስቲያን ስንገባ በጣም መጠንቀቅ ይኖርብናል። እነዚህም ዝግጅቶች፦

**ሀ. የልብ ዝግጅት**

ልጆች የልቡና ዝግጅት የምንለው ወደ ቤተክርስቲያን ከመግባታችን አስቀድሞ ወደ የት እንደምንሄድ ማወቅና ራስን ማዘጋጀት፣ ልቦናችንን ከክፉ ሐሳብና ምኞት አርቀን በመልካም ነገር መዘጋጀትን ነው።

**ለ. ንጹሕ ልብስን መልበስና ገላን መታጠብ**

ልጆች ቤተ-ክርስቲያን ስንሄድ መቁረብ አለብን አይደል? ስንቆርብ ደግሞ ገላችን ንጹሕ መሆን ይኖርበታል። ታጥበን እና ንጹሕ ልብስ ለብሰን ስንሄድ አምላካችን እግዚአብሔር ንጹሕ መሆኑን እየመሰከርን ነው። ሁሉም ሰው ንጹሕ ነገር ሲያይ ደስ እንደሚለው ሁሉ አምላካችን ደግሞ ንጹሕ ስንሆን እንዴት ደስ እንደሚለው ግልጽ ነው ስለዚህ ምን ማድረግ አለብን ስንል ንጹሕ ሆኖ መምጣት ይኖርብናል ማለት ነው።

**ሐ. ነጠላ መልበስ**

ነጠላ ነጭ ነው፤ ነጠላ ለብሰን ቤተክርስቲያን እንደገባነው ሁሉ ዓለም ሲያልፍ አምላካችን እኛ ልጆቹን ወደ መንግሥተ ሰማያት ስንግባ ነጭ ልብስ ያለብሰናል። ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ እያለ ነጭ ልብስ ለብሶ ነው ያደረገው። ስለዚህ እርሱን ለመምሰል ለእርሱ ያለንን ፍቅር ለማሳየት ወደ ቤተመቅደስ ስንመጣ ጸዓዳ (ነጭ) ነጠላ መልበስ አለብን። ነጠላውን ስንለብስ እንዴት መልበስ አለብን? በትዕምርተ መስቀል አመሳቅለን (መስቀለኛ ለብሰን) መሄድ አለብን። እንደዚህ ለብሰን ስንሄድ ጠላት ሰይጣን መስቀል ስለማይወድ ነጠላውን ሲያይ ልክ እንደ ጢስ ወዲያው በኖ ይጠፋል።

### መ. ለእግዚአብሔር ሥጦታ ይዞ መምጣት

ሰው ሁሉን የሰጠው ፈጣሪው እግዚአብሔር ዘንድ ሲመጣ ካገኛት ገቢው ላይ ለእግዚአብሔር ሥጦታ ይዞ መምጣት ይጠበቅበታል:: ለምሳሌ ጧፍ፣ ፩ ጧፍ ይዘን ልንመጣ ከቻልን ይዘን መምጣት ይኖርብናል ፤ይህ ግን ከቤተሰብ አቅም በላይ ከሆነ ማስቸገር የለብንም::



ሥዕል ፩ ስጦታ (መባ) ይዞ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄድ ሕፃን

## ፩.፩.፪ ቤተ መቅደስ ስንገባ ልናደርጋቸው የማይገቡ ነገሮች

### ሀ. ጫማ አድርገን መግባት የለብንም፡፡


ለምን አትሉም? ነቢዩ ሙሴ ባንድ ወቅት የአማቱን በጎች እየጠበቀ ሳለ በኮሬብ ተራራ ላይ ድንቅ ነገር አየ፡፡ ያየው እሳት እና ሐመልማል ነበር፡፡ እሳቱና ሐመልማሉ ተስማምተውና ሳይጠፋፉ አየና ጠጋ ብሎ በቅርበት ሊመለከት ሲል እግዚአብሔር አምላክ ሙሴን “ሙሴ፤ ሙሴ ያለህባት ቦታ የተቀደሰች ናትና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ አለው፡፡” ዘጸ ፫፥፩ ሙሴም ለእግዚአብሔርና ለቦታው ክብር ለመስጠት ሲል ጫማውን አወለቀ፡፡ ከዚህ በመነሳት እኛም ወደ ቤተ መቅደስ ስንገባ እግዚአብሔር ስላለ እንዲሁም ቦታው የተቀደሰ ስለሆነ ጫማችንን ማውለቅ ይኖርብናል፡፡

### ለ. ምግብና መጠጥ ይዞ አለመግባት

ይህ ማለት ለምሳሌ እንደ ብስኩት፣ ዳቦ፣ ወተት፣ ጭማቂ የመሳሰሉት ነገሮችን ይዞ መግባት ክልክል ነው፡፡ ምክንያቱም በቤተ መቅደስ የሚበላውና የሚጠጣው የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋው ክቡር ደሙ ብቻ ነው እንጂ ሌሎች ምግቦች አይገቡም፡፡

### ሐ. የመኝታ ልብስና ተገቢ ያልሆነ አለባበስ ለብሶ  አለመምጣት

ልጆች ይህ ለምን እንደተከለከለ ታውቃላችሁ? የሌሊት ልብስ በላብ ስለ ሚቆሽሽ ነው፡፡ ሌላው የምንለብሳቸው ልብሶች ረጃጅም ልብሶች ሰውነትን የማያሳዩ፣ ወንድሞች ጥሩ ሱሪ በቀበቶ ታጥቀው ከላይ ደግሞ ሰውነት የማያሳይ ልብስ መልበስ ጸጉርን መቆረጥ ያስፈልጋል፡፡ ነጠላ መልበስም አለብን ነገር ግን ጸጉራችንን መሸፈን የለብንም፡፡ እህቶች ደግሞ የምንለብሰው ረጅም ቀሚስ ከላይም ሰውነት የማያሳይ ልብስ እንዲሁም ሙሉ ሰውነታችንን የሚሸፍን ነጠላ መልበስ አለብን፡፡ ጸጉራችንን ቢቻል ነጭ በሆነ ሻሽ ካልተገኘም በንጹሕ ጨርቅ ማሰር ከዛም ነጠላውን ከላይ መደረብ ይኖርብናል፡፡



ሥዕል ፬ ፡ ነጠላ በሥርዓት ለብሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ የተዘጋጁ ሕፃናት

## ፩.፪ ቤተክርስቲያን የመሳለም ሥርዓት

ልጆች ቤተ ክርስቲያን ስንሄድ ምን ማድረግ እንዳለብን አወቅን አይደል? አሁን ደግሞ እንዴት መሳለም እንዳለብን የመሳለም ሥርዓቱ ምን እንደሚመስል እንነጋገራለን።


### ሀ. በትእምርተ መስቀል ማማተብ

በሩ ላይ ስንገባ ማማተብ አለብን። ስናማትብ ስመ ሥላሴን እንጠራለን፤ በጣቶቻችን መስቀል እንሠራለን በዚህም እንባረካለን፤ ጠላት ዲያብሎስ ደግሞ እግዚአብሔር ሲመሰገን መስማትና መስቀል ማየት አይወድም። ስናማትብ ሐሳባችን እንዲሰበሰብ እና ደስ ብሎን ለጸሎት እንድንዘጋጅ ያደርገናል። ካማተብን በኋላ መስገድ ይገባናል፤ በሩንም መሳለም ይገባናል።



**የተግባር ልምምድ**

እባክዎ መምህር ለተማሪዎች የማማተብ ሥርዓትን በተግባር ያሳዩአቸው። መምህራችሁ በሚያሳዩአችሁ መሠረት በትእምርተ መስቀል አድርጋችሁ በሥርዓት አማትቡ።



ሥዕል ፫ ፡ በትዕምርተ መስቀል የሚያማትብ ሕፃን

**ለ. ካህን ጋር ቀርቦ መስቀል መሳለም**

ከቤታችን ጀምሮ አባቶች ካህናትን በመንገዳችን፣ በቤተክርስቲያን በር ላይ እንዲሁም በግቢ ውስጥ ካገኘናቸው የካህናትን ጉልበት በመሳም በመስቀላቸው መባረክ ይኖርብናል::

## ፩.፫ የስግደት ሥርዓት

ስግደት ማለት ምን ማለት ነው?

ስግደት የሚለው ቃል ትሕትና፣ ዝቅ ማለት፣ ማጐንበስ፣ መንበርከክ፣ መደፋት፣ በግንባር መውደቅ፣ ግንባርን ምድር አስነክቶ መሬት ስሞ መመለስ ማለት ነው::

ልጆች በቤተክርስቲያናችን ስግደት የአምልኮና የጸጋ እንዲሁም የአክብሮት ተብሎ በሦስት ይከፈላል::


፩. የአምልኮ ስግደት ለእግዚአብሔር ብቻ የሚቀርብ ሲሆን

፪. የጸጋ ስግደት ደግሞ እግዚአብሔር ላከበራቸው ቅዱሳን ሰዎችና መላእክት የሚቀርብ ነው::

፫. የአክብሮት ስግደት ደግሞ ታላላቆቻችንን እናት አባቶቻችንን ከወገብ ጎንበስ ተብሎ ጉልበት መሬት ሳይነካ የሚሰጥ ሰላምታ ነው

እንደ ቅድስት ቤተክርስቲያን ሥርዓት ወደ ቤተክርስቲያን ስንገባ ቢያንስ ሦስት ጊዜ መስገድ አለብን:: በምንሰግድበት ጊዜ ቅዱሳት ሥዕላት ክብር የሚገባቸው ናቸውና ለቅዱሳት ሥዕላትም እንደየ ሥዕሉ ባለቤት የጸጋ ስግደትን እንሰግዳለን:: ስናከብራቸው ከሥዕላቱ ባለቤቶች በረከትን እናገኛለን፤ ያከበራቸውን እግዚአብሔርን ደስ እናሰኘዋለን:: ስለዚህ የአክብሮት ስግደት እንሰግድላቸዋለን:: ልጆች ቤተክርስቲያንን ስንሳለም መስገድ ተገቢ ነው:: ስንሳለም እንዲህ እያልን ነው፡- “ሰላም ለኪ ቅድስት ቤተክርስቲያን፣ አምሳለ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት፣ ማኅደረ መለኮት፣ ትርጉሙም (የመለኮት ማደርያ የሰማያዊት ኢየሩሳሌም አምሳያ የሆንሽ ቅድስት ቤተክርስቲያን ሰላም እልሻለሁ) ማለት ነው::

ቤተክርስቲያን “...ምስአል ወምሥጋድ” (መሥገጃ መለመኛ) እንላታለን ይህን ማለታችን በቤተክርስቲያን መስገድ እንደሚገባን የሚጠቁም ነው፡ መስቀልን፣ መጽሐፍ ቅዱስን፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን፣ ቅዱሳት ሥዕላትን፣ ቅዱሳት ቦታዎችን፣... ወዘተ ስንሳለም በተመሳሳይ መልኩ መስገድ ተገቢ ነው::



ሥዕል ፬ ፡ ወደ ቤተክርስቲያን ከመግባቱ በፊት የሚሰግድ ሕፃን

**የተግባር ልምምድ**

እባክዎ መምህር ሰላምታውን በቃላቸው እንዲይዙ ደጋግመው በማስጠናት ይርዷቸው፡፡

## ፩.፬ ነጠላ የመልበስ ሥርዓት

ነጠላ ማለት ነጭ የሆነ ሰውነታችን ላይ የምንደርበው ልብስ ነው፡፡ ማንም ሰው ቤተክርስቲያን ሲሄድ ነጠላ መልበስ ይገባዋል፡፡ ስለዚህ እኛም በቤታችን ነጣላ ሊኖረን ይገባል፡፡

ልጆች ነጠላ ምን አይነት መሆን አለበት?


ነጭ ሊሆንና አጭር ያልሆነ ሰውነታችንን የሚሸፍን መሆን አለበት፡፡

ነጠላችንን የት የት እንለብሰዋለን?

ቤተክርስቲያን ስንሄድ፣ ለበዓል፣ ስንቆርብ፣ ስንጸልይ በዚህ ጊዜ ነጠላ ማድረግ አለብን፡፡

ነጠላ እንዴት መልበስ አለብን?

- ነጠላውን እንነጥለዋለን፡
- ጥለቱን በግራ እና በቀኝ አድርገን በወገባችን በኩል እናደርገዋለን፡
- በወገባችን ያመጣነውን ነጠላ ከትከሻችን እስከ እግራችን ጫፍ እናለብሰዋለን፡፡
- በቀኝ በኩል የተረፈውን ነጠላ ወደ ፊት አምጥተን የግራ ትከሻችን ማልበስ፡፡
- ከዚህ ቀጥሎ በግራ በኩል ደግሞ የተረፈውን ነጠላ ወደ ቀኝ ትከሻችን ማልበስ፡፡
- ከቀኙ ወደ ግራው ነጠላችንን ማድረጋችን ከገነት ወጥተን በኃጢአታችን ምክንያት ሲኦል ገባን ማለት ነው
- ከግራ ወደ ቀኝ ደግሞ ነጠላችን መስቀል ይሠራልናል ይህንንም ማድረጋችን ደግሞ ሲኦል የነበርን የሰው ልጆች አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ከሲኦል አወጣን ወደ ገነት መለሰን ስንል ነው፡፡



ሥዕል ፫ ፡ ነጠላ በሥርዓት የለበሱ ሕፃናት

## የተግባር ልምምድ

እባክዎ መምህር የነጠላ አለባበስ ሥርዓትን ለተማሪዎች በተግባር ያሳዩ:: እናንተም ሕጻናት መምህራችሁ ባሳዩአችሁ መሠረት ነጠላችሁን በሥርዓት አጣፍታችሁ ልበሱ::

ወንዶች እንዴት ነጠላ ይለብሳሉ ስንል ወንድሞች ጸጉራቸውን ገልጠው ሳይከናነቡ ሊሆን ይገባል:: ስለዚህ ለወንድሞች ፀጉርን ማሳደግ አይገባም:: እኅቶች ደግሞ ፀጉራቸውን መከናነብ በነጠላው መሸፈን ሻሽ አስሮ መምጣትም ያስፈልጋል ማለት ነው::

## የተግባር ልምምድ

ልጆች በዚህ ምዕራፍ የተማራችሁትን ለቤተሰቦቻችሁ ተናገሩ::

# የምዕራፉ መልመጃዎች

## ትእዛዝ አንድ ፦ ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ሐሰት በማለት መልሱ

፩. ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንገባ ነጠላ ማድረግ አያስፈልግም።

፪. በቅዳሴ ጊዜ መውጣትና መግባት እንዲሁም መረበሽ የቤተክርስቲያን ሥርዓት ነው።

፫. የአምልኮ ስግደት የሚሰገደው ለአምላካችን ሲሆን የጸጋ ስግደት ለቅዱሳን ይሰገዳል።

## ትእዛዝ ሁለት ፦ ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ።

፬. ከሚከተሉት አንዱ ቤተክርስቲያን ስንገባ የምናደርገው ነው።


ሀ. መሳለም ለ. መስገድ

ሐ. መጸለይ መ. ሁሉም መልስ ነው

፭. ከሚከተሉት አንዱ የስግደት ዓይነት ነው?

ሀ. የአምልኮ ለ. የጸጋ

ሐ. ሀ እና ለ መ. መልሱ የለም



ከላይ የተሰጠውን ሥዕል ቀለም በመጠቀም አቅልሙ!

# ምዕራፍ ሁለት
# ሥርዓተ ቅዳሴ

## የምዕራፉ ዓላማ

### ልጆች ይህንን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ


- የቅዳሴን ምንነት እና ጥቅም ያውቃሉ፣
- በቅዳሴ ጊዜ የሚደረጉና የማይደረጉ ነገሮችን ይለያሉ፣
- ልጆች ይህንን ትምህርት ተምረው በተማሩት መሠረት ያስቀድሳሉ፣
- ማስቀደስ ያለባቸው በጥንቃቄና በሥርዓት መሆን እንደሚገባው ያውቃሉ።

## ቁልፍ ቃላት

- ቍርባን፡- የክርስቶስ ሥጋና ደም
- ቅዳሴ፡- ምሥጋና

## የማስጀመሪያ ጥያቄዎች

ልጆች ቅዳሴ አስቀድሳችሁ ታውቃላችሁ? መቼ መቼ?



ሥዕል ፯ ፡ በጸሎተ ቅዳሴ ወንጌል ሲነበብ

## ፪.፩ የቅዳሴ ሥርዓት

ልጆች ቅዳሴ ማለት ቀደሰ ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ሲሆን አመሰገነ፣ ባረከ፣ አከበረ፣ ለየ፣ ለእግዚአብሔር መርጦ ሰጠ ማለት ነው።
ሥርዓት ማለት ደግሞ ሠርዐ ሠራ ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ነው። ትርጉሙ ሕግ ደንብ አሠራር ማለት ነው።

በአንድ ላይ አድርገን ስናነበው የምሥጋና ሥርዓት ማለት ነው የሚመሰገነው ደግሞ እግዚአብሔር ነው።

ቅዳሴ፡

- በሰማይ የሚገኘውን ሥርዓት በምድር መተግበር ነው።
- ቊርባን የሚቀርብበት እግዚአብሔርን የምናመልክበት ሥርዓት ነው።
- በደስታ የምናከናውነው እግዚአብሔርን የምናመልክበት ጸሎት ነው።

ቅዳሴ አባቶች ካህናት እና ምእመናንን ያሳተፈ የምሥጋና ሥርዓት ነው። ልጆች ካህን ለመሆን ቅዳሴ ለመቀደስ ትፈልጋላችሁ? ስለዚህ ዘወትር ለቅዳሴና ለመንፈሳዊ ትምህርት ትኩረት ልትሰጡ ይገባል። እሑድ ጧት፣ ቅዳሜ ጧት ትምህርት በሌለን ቀናቶች ከቤተሰቦቻችን ጋራ ሆነን ልናስቀድስ ይገባናል።


## ፪.፪ በቅዳሴ ውስጥ መሳተፍ የሚገባቸው እነማን ናቸው?

ካህናት፡- እነርሱም ጳጳሳት፣ ቀሳውስት፣ ዲቆናት በመቀደስ ምእመናን በማስቀደስ ይሳተፋሉ ከሁሉ በላይ አምላካችን የሚገኝበት እመቤታችን ቅድስት ማርያም የምትገኝበት መላእክት የሚገኙበት ሁሉም ቅዱሳን እንደተሰጣቸው ክብር የሚገኙበት ጸሎት ነው ስለዚህ ስናስቀድስ ብዙ በረከት እናገኝበታለን።

## ፪.፫ በቅዳሴ ወቅት ስለሚደረጉ ሥርዓቶች

- ቀጥ ብሎ ማስቀደስ፤
- በፍርሃት ማስቀደስ፤

- ነጠላ ለብሶ ማስቀደስ፤
- መደማመጥ፤
- ንጹሕ ልብስ መልበስ፤
- ገላን ታጥቦ መምጣት፤
- ሥርዓቱን በዐይናችን መከታተል በጸሎቱ ላይ ተሰጥዖ መመለስ ያስፈልጋል፣
- መቊረብ ፦ ለመቊረብ ቅዳሴው ከመጀመሩ በፊት መገኘት ይገባል ቅዳሴ ከተጀመረ በኋላ መጥቶ መቊረብ አይፈቀድም፣
- ቅዳሴ እስከሚያበቃ መቆየት፤
- ቅዳሴ ሰዓት ላይ የሚታዘዙትን ትዕዛዛት መፈጸም፤ ስገዱ ሲባል መስገድ ተነሱ ሲባል ንቅት ብለን በደንብ ሥርዓቱን መከታተል፤
- ምንባባትን በትኩረት መስማት።



ሥዕል ፲ ፡ ምእመናን ቅዳሴ ሲያስቀድሱ

## ፪.፬ በቅዳሴ ወቅት የሚከለከሉ ድርጊቶች

- በቅዳሴ ሰዓት መረበሽ አይፈቀደም። ይህም መሯሯጥ መጮህ ቤተሰብን ማስቸገር ምእመናንን ማስቸገር ጮክ ብሎ ማውራት እነዚህን ጥሩ ያልሆኑ በቅዳሴ ሰዓት የማይፈቀዱ ነገሮች ናቸው፤
- ከቤተ መቅደስ መውጣትና ወደ ቤተ መቅደስ መግባት አይቻልም፤
- ምራቅን መትፋት ነውርና ክልክል ነው፤
- ቅዳሴ የኅብረት ጸሎት ስለሆነ የግል ጸሎት ማድረግ አይገባም፤
- ዝም ብለንም መቆም አይገባንም፤
- ምግብን መጠጦችን ይዞ መግባት ክልክል ነው፤
- ቅዳሴን ሳይጨርሱ አቋርጦ መውጣት ክልክል ነው።

**የተግባር ልምምድ**

ልጆች በዚህ ምዕራፍ የተማራችሁትን በተግባር ከቤተሰቦቻችሁ ጋር በመሆን ከሥርዓተ ቅዳሴ ተካፋይ ሁኑ።

### የምዕራፉ መልመጃዎች

ትእዛዝ አንድ፦ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ስሕተት የሆነውን ሐሰት በማለት መልሱ።

፩. ቅዳሴ ለሰው ልጅ እጅግ ጠቃሚ ነው።
፪. በቅዳሴ ሰዓት መንቀዥቀዥ አለብን።
፫. ቍርባን የምንቆርበው ቅዳሴ ካስቀደስን በኋላ ነው።
፬. ወንድሞች ቅዳሴ ሲያስቀድሱ ነጠላ ማድረግ የለባቸውም።
፭. የቤተክርስቲያን ዋናውና ትልቁ ምሥጢር ጸሎተ ቅዳሴ ነው።

## ትእዛዝ ሁለት፦ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሀ ሥር ያለውን ለ ሥር ካለው ጋራ አዛምድ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ፩. ቅዳሴ | ሀ. ሕግ ፣ደንብ፣ አሰራር |
| ፪. ሥርዓት | ለ. ጳጳሳት፣ ቆሞሳት ቀሳውስት ዲያቆናት |
| ፫. ካህናት | ሐ. ቅዳሴ የሚቀደስበት ቦታ |
| ፬. ቤተክርስቲያን | መ. ቀደሰ፣ ለየ፣ መረጠ፣ አመሰገነ |

## ትእዛዝ ሦስት፦ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ።

፩. በቅዳሴ ወቅት ማድረግ ያለብን ነገር

ሀ. በደንብ ማስቀደስ　　ሐ. መረበሽ

ለ. ሥርዓቱን መከታተል　　መ. ሀእናለ

፪. በቅዳሴ ወቅት ማድረግ የሌለብን

ሀ. መረበሽ　　ሐ. ምግብ ይዞ መግባት

ለ. መሯሯጥ　　መ. ሁሉም

፫. ሥርዓት ማለት የቃሉ ትርጉም

ሀ. ሕግ　　ሐ. ለየ

ለ. ቀደሰ　　መ. ለመነ

፬. ቅዳሴ የሚቀድሱት እነ ማን ናቸው?

ሀ. ምእመናን　　ሐ. ሁለቱም

ለ. ካህናት　　መ. መልስ የለም

# ምዕራፍ ሦስት
# ቅዱስ መስቀል

## የምዕራፉ ዓላማ

**ልጆች ይህንን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ**

- ቅዱስ መስቀል ምን እንደሆነ ያውቃሉ ፤
- በመስቀል ምን እንዳገኙ ይገነዘባሉ ፤
- ለመስቀል የሚገባውን ክብር መሥጠት እንዳለባቸው ይገነዘባሉ ።

## ቁልፍ ቃላት

- ማዕተብ፡- ምልክት(መለያ)
- አርማ፡- መለያ

## የማስጀመሪያ ጥያቄዎች

ልጆች መስቀል በአንገታችሁ ለምን እንደምታስሩ ተናገሩ

## ፫.፩ መስቀልና ክብሩ

ልጆች መስቀል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ተሰቅሎ ያዳነበት የክርስቲያኖች መለያ ምልክት ነው፡፡

ምልክታችን ስለሆነ በአንገታችን እናስረዋለን፣ ቤተክርስቲያን ጉልላት ላይ እናደርገዋለን፣ ካህናት አባቶች ሁሌም በእጃቸው ይይዙታል እኛንም ያሳልሙናል፡፡ ልጆች ጠላታችን ሰይጣን መስቀልን ይፈራል፡፡

ልጆች መስቀል ለእኛ፡

- መስቀል ኃይላችን ነው፦ ሰይጣንን እናባርርበታለን የሠላም ምልክታችን ነው፡፡
- መስቀል ቤዛችን ነው፦ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ አድኖናል፡፡
- መስቀል የነፍሳችን መዳኛ ነው፦ ክርስትና የምንነሳውና የምንጠመቀው ውኃው በመስቀል ተባርኮ ነው፡፡

## ፫.፪ መስቀል መሳለም (መሳም)

መስቀል ጌታችን መድኃኒታች ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ ቀድሶታል፡፡ ስለዚህ ቅዱስ ነው እኛም ስንሳለመው እንቀደስበታለን፡፡ ልጆች መስቀል ትሳለማላችሁ? መስቀል የምንሳለመው ከቀሳውስት አባቶች ነው ስንሳለም ‹‹ይፍቱኝ›› እንላለን ካህኑ ‹‹እግዚአብ|ሔር ይፍታህ›› ብለው በመስቀል ይባርኩናል፡፡

## ፫.፫ መስቀል በአንገታችን ለምን እናስራለን? ማዕተብ

ማዕተብ ማለት ምልክት ማለት ነው፡፡ ልጆች መስቀልን በአንገታችን የምናስረው፦

- የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልጆች መሆናችንን ለመግለጽ ነው፡፡
- መስቀል ሰይጣንን የሚያርቅልን የመዳናችን ምልክትም ስለሆነ በአንገታችን እናስራለን፡፡
- በአንገታችን ማሰራችን ሰው አንገቱን ከተቆረጠ እንደሚሞት ከመስቀሉ አንለይም ለማለት ነው፡፡



ሥዕል ፯ ፡ መስቀል የሚያሳልሙ ካህን እና ይፍቱኝ የሚል ምእመን

## የተግባር ልምምድ

ተማሪዎች በአንገታችሁ ያሠራችሁትን ማተብ በመቆም ለመምህራችሁ አሳዩ (እባክዎ መምህር ተማሪዎች ማዕተብ ማሰራቸውን ያረጋግጡ)።

## የምዕራፉ መልመጃዎች

### ትእዛዝ አንድ፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ስሕተት የሆነውን ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

፩. መስቀል ኃይላችን ነው፡፡

፪. እኛ ክርስቲያኖች በአንገታችን ላይ መስቀልን ማሰር አለብን፡፡

፫. መስቀል የክርስቲያኖች ምልክት ነው፡፡

፬. ጠላት ሰይጣን መስቀል አይፈራም፡፡

### ትእዛዝ ሁለት፡- ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

፩.መስቀል ምናችን ነው?

ሀ. ኃይላችን ሐ. የሚያጸናን

ለ. መመኪያችን መ. ሁሉም

፪. መስቀል የምንሳለመው ከማን ነው

ሀ. ከዲያቆናት ለ. ከቀሳውስት

ሐ. ከምዕመናን መ. መልሱ የለም

፫. መስቀል አንገታችን ላይ ስናደርግ ምን ይባላል?

ሀ. ጌጣጌጥ ለ. ገመድ

ሐ ማዕተብ መ. መልስ የለም

፬. ስለ መስቀል ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. የእግዚአብሔር ክብር የታየበት ነው፡፡

ለ. ጠላት ሰይጣን የተሸነፈበት ነው፡፡

ሐ. ጠላት ሰይጣን የወደቀበት ነው፡፡

መ. ለኛ መመኪያችን ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት
# ሥርዓተ ቁርባን

## የምዕራፉ ዓላማ


**ልጆች ይህንን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ**

- ቁርባን ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ይገነዘባሉ፣
- ሥርዓተ ቁርባን እንዴት መፈጸም እንዳለባቸው ያውቃሉ፣
- ከቆረቡ በኋላ ማድረግ ያለባቸውንና ማድረግ የሌለባቸውን ይለያሉ።

## የማስጀመሪያ ጥያቄዎች

ልጆች ቅዱስ ቁርባን ተቀብላችሁ ታውቃላችሁ? እየተነሳችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

ልጆች የቁርባን መስራቹ አምላካችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ቍርባን ማለት የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም በንጹሕ ሰውነት ምንም ሳናጠፋ ኃጢአት ሳንሠራ ካጠፋንም ንስሓ ገብተን የምንቀበለው መንፈሳዊ ምግብ ነው:: እኛም ሕጻናት ዘወትር በየወሩ ወይም በየሳምንቱ የንስሓ አባቶቻችንን እና ቤተሰብ በማማከር ልንቆርብ ያስፈልጋል:: ምክንያቱም ካልቆረብን ከአምላካችን ጋር አብረን አንኖርም:: ከሱ ጋር አብረን ለመኖር መቍረብ ይገባናል::



ሥዕል ፰ ፡ ሕፃናት በቤተ መቅደስ ቅዱስ ቍርባን ሲቀበሉ

## ፬.፩ ሥርዓተ ቍርባን በቤተ ክርስቲያን

ቍርባን የሚያቆርቡን፡- ካህናት ሲሆኑ እነዚህም ጳጳሳት፣ ቀሳውስት ቅዱስ ሥጋውን ያቀብሉናል:: ክቡር ደሙን ደግሞ ዲያቆናት ያቀብሉናል::

መቍረብ ያለበት

- በሥላሴ ያመነና ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የሆነ ብቻ ነው::
- ሁሉም ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የሆነ ሰው ንስሓ ገብቶ ሊቆርብ ይገባዋል::
- ሳይጸሙ ንጹሕ ሳይሆኑ ንጹሕ ልብስ ሳይለብሱ መቁረብም አይቻልም:: ስለዚህ ለመቁረብ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል::

ስንቆርብ በደረጃ ነው ሥጋወ ደሙ ልክ ለምእመናን ማቀበል እንደተጀመረ በመጣደፍ ሰውን እየገፋን መቀበል የለብንም:: ተራችንን ጠብቀን መሬት ወድቀን በመስገድ ቀስ ብለን ሳንጋፋ ልንቀበል ያስፈልጋል:: ከመቍረባችን በፊት አፋችን ውስጥ ምንም ነገር ሊገባ አያስፈልግም:: ቅዳሴ ሳያስቀድሱ መቍረብ አይቻልም:: ልጆች ለመቍረብ ቅዳሴ ሳይጀመር ቤተክርስቲያን መገኘት ያስፈልጋል:: ቅዳሴ ከተጀመረ በኋላ መጥቶ መቍረብ አይፈቀድም ስለዚህ ለመቍረብ  የፈለገ ሁሉ በጠዋት ተነስቶ "አሐዱ ሳይባል ቤተክርስቲያን መግባት አለበት:: ልጆች የሚቆርብ ልጅን እግዚአብሔር ይወደዋል!



ሥዕል ፱ ፡ ቅዱስ ቍርባን የተቀበለ ልጅ

## ፩.፪ እንዴት መቍረብ እንዳለብን

### ፩.፩.፩ ከመቍረብ በፊት ስለምናደርጋቸው ጥንቃቄዎች

- ከመቍረባችን በፊት ንጹሕ መሆን አለብን። ገላችንን፣ ልብሳችንን በማጠብ በንጽሕና መዘጋጀት
- መጾም አለብን
- ቅዳሴ ከመጀመሩ በፊት ተገኝቶ ማስቀደስ አለብን።
- ከቅዳሴ በፊት ከቆሰልን ወይም ከደማን ቅዳሴ መግባት ስለማንችል መጠንቀቅ አለብን።
- ነጠላ ለብሰን መምጣት ይገባናል።

### ፩.፪.፪ ስንቆርብ የምናደርጋቸው

- ካህናት ለማቁረብ ከቤተመቅደስ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙን ይዘው ሲወጡ መስገድ፣
- መስቀል መሳለም፣
- ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን በጥንቃቄ መቀበል፣
- ሥጋ ወደሙን እንደተቀበልን አፋችን ላይ ሳናቆይ ወዲያውኑ መዋጥ፣
- ሥጋ ወደሙ እንዳይነጥብም ቶሎ በነጠላችን አፋችንን መሸፈን ፣
- ምንም ዓይነት ወሬ ከማንም ጋር አለማውራት፣
- ቅዳሴ ጠበል መጠጣት፣
- ትንኝ ፣ ቆሻሻ ፣ አቧራ ወደ አፍና አፍንጫችን እንዳይገባ አፍንና አፍንጫችንን በንጹሕ ልብስ ወይም ነጠላ መሸፈን፣
- እግዚአብሔር አምላክን እንድንቆርብ ስላደረገን ማመስገን (ስብሐት ማለት) ፣
- ከዛም ቅዳሴው እስኪያልቅ ድረስ ባለንበት መቆየት ወዲያ ወዲህ አለመንቀዥቀዥ፣ ወደ ቤት ሂዱ ብሎ ዲያቆኑ እስኪያውጅ ድረስ ከቤተ ክርስቲያን አለመውጣት• ቅዳሴ አልቆ ወደ ቤታችን እንድንሄድ ዲያቆኑ በሰላም ወደየ ቤታችሁ ሂዱ ብሎ ሲያሰናብተን በጥንቃቄ ሳንሯሯጥ ወደ ቤታችን መሄድ።

### ፩.፪.፫ ከቆረብን በኋላ የምናደርጋቸው

- ቆሻሻ አለመንካት፣
- ቤት ከሄድን በኋላ አርፎ ቤት ተቀምጦ መንፈሳዊ ነገሮችን ማየትና መስማት፣
- ቤተሰብን አለማስቸገር አለመረበሽ፣
- ምግብ ከበላን በኋላ የምንፈልገውን ነገር ድምጻችንን ቀንሰን መናገር፣

- ምራቅ አለመትፋት፤ ምግብ ተመግበንም እጃችንን አለመታጠብ አፋችንንም አለመጉመጥመጥ፣
- ልብስ አለመቀየር፣
- ውኃም ምግብም በመጠኑ መመገብ፤ ሳናበዛ መመገብ ፣
- አለማልቀስ፤ አለመጣላት፤ ክርክር ከሰው ጋር አለማድረግ ፣
- ለመጠጣት ካልሆነ በስተቀር ውኃ አለመንካት፣
- ከዘፈን ጫጫታ ካለበት መዝናኛ ከሆኑ ነገሮች እራስን ማሸሽ ፣
- ጥፍር መቁረጥ፣ ጸጉርን መላጨት ሰውነትን መታጠብ አይገባም፣
- ተልጠው የሚበሉ፣ ታኝከው የሚተፉ ነገሮችን በዕለቱ አለመመገብ ለምሳሌ ሙዝ፣ ሸንኮራ ...

ስለዚህ ከነዚህ ይልቅ መዝሙር መስማት፤ ትምህርት መስማት፤ መጽሐፍ ቅዱስንና መንፈሳዊ መጻሕፍትን ማንበብ እና ሌሎች መንፈሳዊ ነገሮችን ወላጅን እያስፈቀዱ ማከናወን ይገባል። ስለዚህ መቁረብ ካለብን እነዚህን ነገሮች ሁል ጊዜ ልናደርግ ይገባል።

## ፬.፫ ሥጋ ወደሙ መቀበል (መቁረብ) ለሰው ልጅ የሚሰጠው ጥቅም

- ጥበብን ይገልጣል፣
- ልብን ብሩህ ያደርጋል፣
- ታጋሽ ያደርጋል፣
- ጎበዝ ለሰው የሚያስብ ሰው ያደርጋል፣
- ለሥጋችንም ለነፍሳችን መድኃኒት ይሆናል፣
- መንግሥተ ሰማያት መግቢያ ይሆናል፣
- ክርስቶስ አምላካችንን ከእኛ ጋር እንዲሆን ያደርጋል፣
- ሰውነታችን ሁሉ የተቀደሰ ይሆናል፣
- ሰላምና ኃይለ መንፈስ ቅዱሰን እናገኛለን።

## የተግባር ልምምድ

መምህር እባክዎ ከዚህ ትምህርት በኋላ ልጆች ተዘጋጅተው እንዲቆርቡ ይዘዙ፡፡ መቁረባቸውንም ከአስተባባሪዎች ጋር በመሆን ይከታተሉ፡፡

### የምዕራፉ መልመጃ

**ትእዛዝ አንድ፡- ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

፩. ስንቈርብ ነጠላ ባናደርግ ችግር የለውም፡፡
፪. ከቈረብን በኋላ ጥፍር መቁረጥ እንችላለን፡፡
፫. ሰውነትን መታጠብ ከቍርባን በፊት የሚደረግ ሥርዓት ነው፡፡
፬. ቍርባን ለክርስቲያኖች አያስፈልግም፡፡

**ትእዛዝ ሁለት ፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች “ሀ” ሥር ያሉትን “ለ” ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ፩.ቍርባን | ሀ. ቆሻሻ መንካት ክልክል ነው |
| ፪.ከቈረብን በኋላ | ለ. ጥበብን ይገልጣል |
| ፫.መቍረብ ያለባቸው | ሐ. የክርስቶስ ሥጋና ደም |
| ፬.የቍርባን ጥቅም | መ.ክርስቲያን የሆነ ሰው ብቻ ነው |

# ምዕራፍ አምስት
# በዓላት

## የምዕራፉ ዓላማ

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ሲያጠናቅቁ**

- የበዓላትን ምንነትና አከባበር ያውቃሉ፣
- የበዓላት ቁጥርን ወይም ብዛታቸውን ያውቃሉ፣
- በተማሩት መሠረት በዓላትን እንደ ቤተክርስቲያን ሥርዓት ያከብራሉ።

## ቁልፍ ቃላት

- ገጸ በረከት፡- ስጦታ
- ሰንበት፡- ቅዳሜና እሑድ
- ዐበይት፡- ታላላቅ
- ንዑሳን፡- ታናናሽ

## የማስጀመሪያ ጥያቄዎች

- ልጆች በዓላትን እንዴት እንደምታከብሩ እየተነሳችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

**ሀ. በዓል ማለት ምን ማለት ነው?**

በዓል ማለት አብዐለ ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን አከበረ፣ አስከበረ፣ ዕለትን በዓል አደረገ የሚል ትርጉም አለው። በቤተክርስቲያን የሚከበሩ ብዙ ቅዱሳን በዓላት አሉ።

**ለ. በዓላት ምንድን ናቸው?**

**፩. የደስታ ዕለት ናቸው**

በዓላት የደስታ ዕለት ለምን ሆኑ? ስንል እግዚአብሔር ያደረገልንን፣ ቅዱሳን ያደረጉትን ነገር እያሰብን ደስ ይለናል። እግዚአብሔር አምላክ ለቅዱሳን ምን ያክል ቅርብ እንደሆነና ለነርሱ ያደረገላቸውን የእርሱን አዳኝነት እያሰብን በደስታ የምንውልበት ዕለት ነው። እኛም የእነርሱን የመንፈሳዊ ሕይወት ጉዞ የምንለማመድበትና ቃል የምንገባበት ዕለት ነው።

**፪. የዕረፍት ቀናት ናቸው**

እግዚአብሔር ድንቅ ነገሮችን የሠራባቸው ስለሆኑ በዕረፍት ሆነን ልናከብራቸው ይገባል። በነዚህም ቀናት ትምህርት ቤት አንሄድም ሥራም አንሠራም ለምሳሌ ብናነሳ ሰንበት፣ የክርስቶስ ልደት፣ የትንሣኤ በዓላትን ማየት እንችላለን። ስለዚህ በእነዚህ ዕለታት ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ ከሥርዓቱ ተካፋይ መሆን እና በጎ ሥራን በማከናወን ልናሳልፋቸው ይገባል። ለምሳሌ የታመሙትን በመጠየቅ የተቸገሩትን በመርዳት፤ ቤተሰቦቻችንን በመታዘዝ

## ፷.፩ የበዓላት አከባበር ሥርዓት በቤተክርስቲያን

እግዚአብሔር እርሱ በሠራው ድንቅ ሥራ በቅዱሳኑ አድሮ ለሠራው ሥራ ሁሉ መታሰቢያ ይደረግለታል። በዓላት በሁለት ይከፈላሉ፤

፩- ዐበይትና

፪- ንዑሳን በዓላት ተብለው።

ዐበይት በዓላት ማለት ዋና ዋና የሆኑ በዓላት ማለት ነው።

**፩.በዓለ ፅንሰት**

ጌታችን አምላካችን የተፀነሰበት ዕለት ነው። ይህም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ያበሰረበት እመቤታችንም ጌታችንን የፀነሰችበት ቀን ነው። ይህም የሚከበረው በመጋቢት ፳፱ ቀን ነው፤ በዚህ ቀን የዐቢይ ጾም ስለሚገባ በጾም ደስታ የለምና የሚከበረው ታኅሣሥ ፳፱ነው።

**፪.በዓለ ልደት**

በዓለ ልደት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት የሚከበርበት ቀን ነው። ጌታችን የተወለደው ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ነው። የተወለደውም በቤተልሔም ከተማ በከብቶች ግርግም ውስጥ ነው። በዓሉ የሚከበርበት ቀን ደግሞ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ነው።

**፫.በዓለ ጥምቀት**

በዓለ ጥምቀት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀበት ዕለት ነው። ይህን ቀን በዓለ ጥምቀት ብለን እናከብራለን። የተጠመቀውም በዮርዳኖስ ወንዝ በመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ እጅ ሲሆን የምናከብረውም ጥር ፲፩ ነው። በቤተክርስቲያናችን በዚህ ዕለት ታቦታት ከቤተ መቅደስ ወጥተው ምድሪቷን ይባርካሉ።

**፬.በዓለ ደብረ ታቦር**

በዓለ ደብረ ታቦር ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ታቦር ላይ ብርሃነ መለኮቱን የገለጠበት በዓል ነው። የሚከበረው ደግሞ ነሐሴ ፲፫ ቀን ነው። በዚህ ዕለት ልጆች የቡሄ መዝሙር እየዘመሩ በደስታ ያከብሩታል።

**፭.በዓለ ሆሣዕና**

የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በአህያና በውርጭላ ኢየሩሳሌም መግባቱን የምናስብበት በዓል ነው። በዓሉ የሚከበረው ከትንሣኤ በዓል አንድ ሳምንት ቀድሞ ባለው እሑድ ነው።

**፯.በዓለ ስቅለት**

በዓለ ስቅለት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን በቀራንዮ ዓደባባይ የተሰቀለበትን ዕለት አስበን የምናከብረው በዓል ነው:: ዕለቱም መስቀሉን እያሰብን በስግደት በጾም የምንውልበት በዓል ነው:: የሚከበረውም ትንሣኤ እሑድ ከመዋሉ በፊት ባለው ዓርብ ነው::

**፰.በዓለ ትንሣኤ**

በዓለ ትንሣኤ የጌታችንን ከሙታን ተለይቶ መነሳቱን የምናከብርበት በዓል ነው:: ይህም ቀኑ በአባቶች ተሰልቶ ጾሙ ካለቀ በኋላ ለ፶ ቀን ይከበራል::

**፱.በዓለ ዕርገት**

በዓለ ዕርገት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማየ ሰማያት ማረጉን አስበን የምናከብረው  በዓል ነው:: በዓሉ የሚከበረውም ትንሣኤ በዋለ በአርባ ቀኑ በዕለተ ሐሙስ ነው::

**፲.በዓለ ጰራቅሊጦስ**

በዓለ ጰራቅሊጦስ የምናከብርበት ዋነኛ ምክንያት ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉበት ቀን ስለሆነ ነው:: የሚውለው ከትንሣኤ በኋላ በ፶ኛው ቀን ነው::

ሌላው በሰንበት (ቅዳሜና እሑድ) ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ ልናከብር ያስፈልጋል:: ሰንበት እጅግ ክብር ያላት በዓል ናት::

ቅዳሜ /የመጀመሪያዋ ሰንበት/፡- የምናከብረውም አምላካችን እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ የጨረሰበት ወይም ያረፈበት ቀን ስለሆነ ነው::

እሑድ /ሰንበተ ክርስቲያን/ ፡- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት የተነሳበት፣ ነፍሳትን ከሲኦል ያወጣበት ቀን ነው::

በሁለቱ ቀናት እንዲሁም ፲፪፣ ፳፩፣ እና ፳፱ መስገድ አይቻልም። ይህም በየወሩ በ፲፪ (የቅዱስ ሚካኤል መታሰቢያ፣ ፳፩ (የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም መታሰቢያ)፣ እና ፳፱ (የጌታችን የልደት መታሰቢያ) ስለሆነ ነው።

## ፳.፪ በዓላትን እንዴት እናክብራቸው

የበዓላትን አከባበር በቤተክርስቲያንና በቤት ብለን እንከፍለዋለን።

### ፳.፪.፩ በዓላትን በቤተ ክርስቲያን ማክበር ያለብን እንዴት ነው?

በቤተክርስቲያን ሥርዓት መሠረት

- ቤተክርስቲያን በመሄድ ልናከብረው ያስፈልገል
- በጸሎት ፣
- መንፈሳዊ ደስታ በመደሰት ፣
- በመቁረብ ፣
- ቅዳሴ በማስቀደስ ፣
- ማኅሌት በመቆም ፣
- ከኃጢአት በመራቅ ፣
- ሰዓታት በመቆም ፣
- በፍጹም ደስታና በምሥጋና ፣
- ታቦት በማክበር ፣
- በመዘመር ፣
- ስግደት በሚሰገድባቸው በስግደት በማይሰገድባቸው ደግሞ ከስግደት በመቆጠብ መሆን አለበት።

### ፳.፪.፪ በቤታችን የምናከብረው እንዴት ነው?

በቤታችን ደግሞ በፍጹም ደስታ በሥነ- ሥርዓት በመመገብ የምንጠጣውንም በመጠኑ በማድረግ ከሁሉ በላይ ሰዎችን የተቸገሩትን በማሰብ መሆን አለበት። ለአምላክ ያለንን ፍቅር በማሳየት እርስ በእርስ በመዋደድ በዓላትን ማክበር ይገባናል።

ስለዚህ በቤት ስናከብር

- የተቸገሩትን መርዳት ፣
- ከቤተሰቦቻችን ጋር ሆነን እግዚአብሔርን በማመስገን ፣
- የተዘጋጀውን ምግብ በአንድ ገበታ (ሳህን) ሁላችንም ተሰባስበን በመመገብ ፣
- ለበዓሉ ክብር ሻማ በማብራት (ግን በጥንቃቄ) ፣
- በደስታና በፍቅር በመጎራረስ ሰውን ዘመዶችን ጎረቤቶችን በመጠየቅ ፣
- ቆርበን ከሆነ ሥርዓት በመጠበቅ እና በመሳሰሉት ማክበር ይገባል።



ሥዕል ፲ ፡
በቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ በማስቀደስ
በዓል የሚያከብር ሕፃን

## ፳.፫ በዓላትን የማክበር ጥቅም

- ከእግዚአብሔርና ቃል ኪዳን ከተሰጣቸው ቅዱሳን በረከት እና ረድኤትን ለማግኘት
- እምነታችንን በሰው ሁሉ ፊት ለመግለጥ፤

### ማጠቃለያ መልመጃ

### ትእዛዝ አንድ፡- ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ሐሰት በማለት መልሱ።

፩.በዓላትን በቤተክርስቲያን ማክበር አያስፈልግም።

፪.በበዓል ወቅት ምግብ ስንበላ በጥንቃቄ መሆን አለበት።

፬.በበዓል መቁረብ አይቻልም።

፭.በ፳፩ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በዓል ላይ መስገድ ይቻላል።

፮.ሆሣዕና በዓል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ ውርንጭላ ኢየሩሳሌም የገባበት በዓል
ነው።

### ትእዛዝ ሁለት ፡- በሀ ሥር ያሉትን ለ ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ፩.በዓለ ልደት | ሀ. ዐበይት በዓላት |
| ፪.በዓለ ጰራቅሊጦስ | ለ. ክርስቶስ ነፍሳትን ያዳነበት |
| ፫.ሰንበት | ሐ. ልክ እንደ ሰንበት የሚከበሩ |
| ፬.፲፪፣ ፳፩፣ ፳፱ | መ. በዓለ መንፈስ ቅዱስ |
| ፭.ዘጠኙ በዓላት | ሠ. የጌታችን ልደት በዓል |

## ትእዛዝ ሦስት ፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ::

፩. የበዓል ጥቅም የሆነው የቱ ነው?

ሀ. በረከት እና ረድኤትን ለማግኘት

ለ. እምነታችንን ለማሳየት

ሐ. ለዕረፍት

መ. ሁሉም

፪.በቤታችን በዓላትን ስናከብር እንዴት መሆን አለበት

ሀ. ንጽሕናችንን ሳንጠብቅ

ለ. የተቸገረ ሰውን ሳንረዳ

ሐ. ለአምላካችን ምሥጋና በማቅረብ

መ. ምግብን ከመጠን በላይ በመብላት

፫.ሰው በቤቱ እና በቤተክርስቲያን ክርስቲያናዊ በዓል ሲያከብር ማድረግ ያለበት?

ሀ. እግዚአብሔርን ያመሰግናል

ለ. የተቸገሩትን ይረዳል

ሐ. ይጸልያል

መ. ሁሉም መልስ ናቸው::

፬.ሰንበት የሚባሉት የትኞቹ ናቸው

ሀ. እሑድ

ለ. ቅዳሜ

ሐ. ዓርብ

መ. ሀእናለ መልስ ናቸው::

፭.በዓለ ደብረ ታቦር መች ይከበራል

ሀ. ሐምሌ፲፫

ለ. ነሐሴ ፲፫

ሐ. ሰኔ፲፫

መ. መስከረም ፩